# የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ

## የስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ድምፅ አሰጣጥ (በሐረሪ፣ በሶማሊ ክልል እና በደቡብ ክልል) እንዲሁም በደቡብ ክልል የሚደረገውን ህዝበ ውሳኔ በተመለከተ የተሰጠ መግለጫ

መስከረም **20 2014**፣ አዲስ አበባ

ስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም በስድስት ክልሎች እንዲሁም በሁለት የከተማ አስተዳደሮች እንደተደረገ የሚታወስ ነው። ሆኖም ከፀጥታ ችግሮች ጋር፣ በመራጮች ምዝገባ እና በምርጫ ቀን ከነበሩ የአሰራር ግድፈቶች እንዲሁም በሌሎች የስምሪት ችግሮች ምክንያት በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች በከፊል አልያም ሙሉ በሙሉ ምርጫ አለመካሄዱ ይታወሳል። በተጨማሪም ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ሊደረግ ቀነ ቀጠሮ ተይዞለት የነበረው የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝበ ውሳኔ በተያዘለት ቀን .አልተደረገም። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዜጎች ድምፅ ባልሰጡባቸው ቦታዎች ምርጫው በጳጉሜ 1 ቀን 2013 ዓ.ም እንደሚደረግ ገልፆ የነበረ ቢሆንም፤ በነሐሴ 17 ቀን 2013 ዓ.ም የድምፅ መስጫ ዕለቱን ወደ መስከረም 20 ቀን  2014 ዓ.ም መተላለፉን እንዳሳወቀ ይታወሳል። በተጨማሪም የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ በሐረሪ እና ሶማሊ ክልሎች እንዲሁም በደቡብ ክልል ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች ብቻ እንደሚካሄድ ቦርዱ ያሳወቀ ሲሆን ይህም  ማለት በቤንሻንጉል፣ አማራ እና ኦሮምያ ክልሎች ድምፅ ያልተሰጠባቸው ቦታዎች ላይ በዛሬው ቀን(መስከረም 20) ድምፅ እንደማይሰጥ ቦርዱ በግዜው አሳውቋል። በመጨረሻም ቦርዱ በተለያዩ ምክንያቶች በደቡብ ክልል በሚገኙ የተለያዩ ዞኖች የድጋሚ ምርጫ እንዲሁም የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝበ-ውሳኔ በተመሳሳይ ቀን እንደሚካሄድ ማሳወቁ ይታወሳል።

በዛሬው ቀን እየተካሄደ ያለው የድምፅ አሰጣጥ ሂደት ለስድስተኛው አገራዊና ክልላዊ ምርጫ ምሉዕነት ያለውን አስፈላጊነት በመገንዘብ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ (CECOE) ከሐረሪ፣ ሶማሊ እና ደቡብ ክልሎች የተውጣጡ 956 ቋሚ እና 37 ተንቀሳቃሽ ታዛቢዎችን መልምሎ በማሰልጠን አሰማርቷል። እነዚህም ታዛቢዎች በሐረሪ፣ ሶማሊ እና ደቡብ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባና ድሬዳዋ ክልሎች በሚገኙ የሐረሪ ብሄራዊ ጉባኤ[1] አባላት ምርጫ ለማካሄድ የተመሰረቱ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። የህብረቱ ታዛቢዎች በምርጫ ቀን ትዝብታቸውን በቀላሉ ለማከናወን የሚረዷቸው በተለያዩ ቋንቋዎች የተዘጋጁት ወጥ መጠይቆች እና አሳሳቢ ኹነት ቅፅ የተሰጣቸው ሲሆን፤ ቋሚ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የሚያዩትን አሰራር ተለይቶ በተሰጣቸውን የታዛቢነት መለያ ቁጥር በመጠቀም በአጭር የፅሁፍ መልዕክት አዲስ አበባ ወደሚገኘው የህብረቱ የመረጃ ማዕከል እያደረሱ ይገኛሉ። ይህ የህብረቱ የምርጫ ዕለት የግማሽ ቀን የትዝብት ሪፖርት እስከተዘጋጀበት ሰዓት ድረስ ሪፖርት ካደረጉ የህብረቱ 941 ታዛቢዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ ችሏል። ነገር ግን በአንዳንድ ምርጫ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች ከሚታየው የስልክ ኔትወርክ መቆራረጥ አንፃር እስካሁን ሪፖርቶቻቸውን ለመላክ ያልቻሉ ታዛቢዎችን ጨምሮ ሁሉም ታዛቢዎቹ ተጨማሪ ሪፖርቶችን ይልካሉ ብሎ ያምናል። በተጨማሪም ህብረቱ ከታዛቢዎች የሚላኩ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ በማጣራት እና በማረጋገጥ የሚገኝ ሲሆን፤ በዚህ መግለጫ ውስጥ የተካተቱት ግኝቶች የድምፅ ቆጠራው ሲጠናቀቅ በሚደርሱት የትዝብት መረጃዎች መሰረት ሊለወጡ የሚችሉ መሆናቸውን ሊገልፅ ይወዳል።

ይህ የህብረቱ የምርጫ ዕለት የግማሽ ቀን የትዝብት ሪፖርት 941 ታዛቢዎች ወደሚታዘቡባቸው የድምፅ ምርጫ ጣቢያዎች ሲደርሱ፣ እንዲሁም የጣቢያዎቹ አከፋፈትና ዝግጅት ከታዘቡ በኋላ በላኳቸው ሪፖርቶች ላይ የተመሰረተ ነው።

- የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ከማለዳው 12 ሰዓት ላይ ለመራጮች ክፍት እንዲሆኑ ይጠበቃል። ይህንን መሠረታዊ የሆነ የምርጫ ሂደት በሚገባ መተግበሩን ለማየት እንዲረዳው ህብረቱ ታዛቢዎቹ ከንጋቱ 11፡30 ጀምሮ በተመደቡበት የምርጫ

[1] የሀረሪ ብሄራዊ ምክር ቤት ድምጽ አሰጣጥ በሀረሪ ክልል ውስጥ እና ውጭ የሚኖሩ የሐረር ተወላጆች 14 መቀመጫ ላለው ምክር ቤት እንዲመርጡ በ1995 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባስተላለፈው ውሳኔ የተመሰረተ ልዩ የምርጫ ሂደት ነው። የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይህ አሰራር ህጋዊ አይደለም ብሎ በፍርድ ቤት ቢከራከርም በኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ፍርድቤት ጥያቄው ውድቅ መሆኑ የሚታወስ ነው።

ጣቢያዎች እንዲገኙ አድርጓል። ታዛቢዎቻችን ከታዘቧቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ96 በመቶዎቹ የምርጫ አስፈፃሚዎች ከንጋቱ 11፡30 ላይ በየጣቢያዎቻቸው ተገኝተዋል። በተጨማሪም 99 በመቶ የታዛቢዎቻችን ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት ከንጋቱ 12፡00 ጀምሮ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለመራጮች ክፍት ሆነዋል።

- በአጠቃላይ ህብረቱ ያሰማራቸው የምርጫ ታዛቢዎች ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጣቸውን  የታዛቢነት መለያቸውን በማሳየት በድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በመግባት መታዘብ ችለዋል። 99% የህብረቱ ታዛቢዎች በተመደቡባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እንደደረሱ ገብተው እንዲታዘቡ ፈቃድ አግኝተዋል። በአንፃሩ በሀረሪ፣ በሶማሊ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ጥቂት የምርጫ ጣቢያዎች እንዲሁም በአዲስ አበባ በአንድ አጋጣሚ ታዛቢዎቻችን የታዛቢነት ፈቃዳቸውን ለጣቢያ ኃላፊዎቹ ቢያሳዩም እንዳይታዘቡ ተከልክለው ነበር። ህብረቱ እነዚህን አስቸኳይ ምላሽ የሚፈልጉ ጉዳዮችን በፍጥነት ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ያሳወቀ ሲሆን፤ በቦርዱ ጣልቃ ገብነት የተጠቀሱት ችግሮች ተፈተው ታዛቢዎቻችን ስራቸውን እንዲቀጥሉ ተደርጓል።

- የመራጮችን ድምፅ የመስጠት መብት በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ፤ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ለሁሉም መራጮች አመቺ በሆነ ቦታ ላይ መቋቋም ይኖርባቸዋል። በህብረቱ ታዛቢዎች ሪፖርት መሰረት፣ ትዝብት ከተደረገባቸው የምርጫ ጣቢያዎች መካከል 96 በመቶዎቹ ለአካል ጉዳተኞች ወይም የመንቀሳቀስ እክል ላለባቸው መራጮች በሚመቹ ስፍራዎች ላይ ተቋቁመዋል። በተመሳሳይ፣ ትዝብት ከተደረገባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች መካከል 97 በመቶዎቹ ለሴቶችም ሆነ ለወንዶች በተመጣጣኝ ሁኔታ አመቺ በሆኑ ቦታዎች ላይ መቋቋማቸውን ታዝቧል።

- የምርጫ አስፈፃሚዎችን በተመለከተ ህብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በአማካይ አራት የምርጫ አስፈፃሚዎች ተገኝተው የነበረ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 37 በመቶ የሚሆኑት ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎች ናቸው። ከዚህ በተጓዳኝ 23 በመቶ በሚሆኑት ህብረቱ የታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ሴቶች በምርጫ ጣቢያ ሀላፊነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ይህ ግኝት የሚያበረታታ ቢሆንም በእያንዳንዱ ምርጫ ክልል ቢያንስ አንድ ሴት የምርጫ አስፈፃሚ እንደምትኖር የምርጫ ቦርዱ ካስቀመጠው አቅጣጫ አንፃር በ12 በመቶ ህብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች አንድም ሴት አስፈፃሚ አለመኖሯ አሳሳቢና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው ብሎ ህብረቱ ያምናል።

- በሰኔ ወር በተካሄደው ብሔራዊና ክልላዊ ምርጫ ወቅት ከተስተዋሉ ችግሮች መካከል አንዱ የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች እጥረት ወይም ጨርሶ አለመኖር ነበር። ይህ ችግር ሰኔ 14 ቀን በተደረገው የድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ ሂደት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አሳድሮ እንደነበርም የሚታወስ ነው። ወደ ህብረቱ ከተላኩ አንዳንድ አሳሳቢ ኹነቶች በስተቀር በዛሬው ቀን ህብረቱ ከሰበሰባቸው ሪፖርቶች መካከል ሁሉም በሚባል መጠን የምርጫ ጣቢያዎች ሲከፈቱ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን፣ የድምፅ መስጫ ሳጥን ማሸግያ፣ የምርጫ ቦርድ ህጋዊ ማህተም፣ የማይጠፋ የጣት ቀለም እንዲሁም የማመሳከርያ ቅፅ የተሟላ እንደነበር ያሳያል። ይሁንና  ህብረቱ በወላይታ ዞን በሚገኝ አንድ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ የመራጮች መዝገብ እንደጠፋ መረጃ የደረሰው ሲሆን ይህን መረጃ በሚያጣራበት ወቅት የምርጫ አስፈፃሚዎች ቃለ ጉባኤ በመያዝ መራጮችን ያለ መዝገብ እያስመረጡ እንደሆነ አረጋግጧል። የዚህን እና ሌሎች ተጨማሪ ክስተቶችን ህብረቱ በማጣራት ላይ ይገኛል። ህብረቱ የድምፅ መስጫ ቁሳቁሶች እስከድምፅ አሰጣጥ ማጠናቀቅያ ድረስ ተሟልቶ መራጮች ድምፅ መስጠት ስለመቻላቸው ተከታትሎ በነገው የመጀመሪያ ደረጃ የምርጫ ትዝብት መግለጫው ላይ እንደሚያቀርብ ይገልፃል።

- ይህ መግለጫ እስከተዘጋጀበት ሰዓት ድረስ ህብረቱ ከሰበሰባቸው መረጃዎች መካከል አንዱ የምርጫ ጣቢያዎች በተከፈቱበት ወቅት በምርጫ ጣቢያዎች ተገኝተው የነበሩ የፓርቲ ወኪሎች ቁጥር ነው። 77 በመቶ ያህል በሚሆኑት ህብረቱ በታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች የፓርቲ ወኪሎች ተገኝተው ነበር።

- ህብረቱ ከዚህ ቀደም በሰኔ 2013ቱ ትዝብቱም ሆነ በዛሬው እለት በመካሄድ ላይ ባለው ምርጫ ለመታዘብ እንደቻለው ከታዩት ክፍተቶች አንዱ ለኮሮና ቫይረስ መከላከል የሚደረጉ የጥንቃቄ እርምጃዎችን መጓደል አንዱ ክፍተት ነው። ይህ

መግለጫ እስከተሰጠበት ሰዓት ድረስ በህብረቱ የተሰበሰቡ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት 68 በመቶ የህብረቱ ታዛቢዎች በተገኙባቸው የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ላይ ያለው ሰልፍ አካላዊ ርቀትን ለማስጠበቅ በከፊል ወይም ጨርሶ የማያስችሉ ናቸው። በተጨማሪም የህብረቱ ታዛቢዎች ከተገኙባቸው የምርጫ ጣቢያዎች 56 በመቶ የምርጫ የጣቢያዎች ውስጣዊ አደረጃጀት አካላዊ ርቀትን ለመጠበቅ የማያስችሉ ወይም በከፊል የሚያስችሉ እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል። ይህም ችግሩ አሁንም ትኩረት የሚሻ መሆኑን ያመለክታል።

ከላይ ከተጠቀሱት የድምፅ መስጫ ዕለት የግማሽ ቀን ሪፖርት ግኝቶች በተጨማሪ፤ ህብረቱ 15 ያህል አሳሳቢ ኹነቶችን በመቀበል አጣርቶ መከሰታቸውን አረጋግጧል። ከላይ ከተዘረዘሩት አሳሳቢ ኹነቶች መካከል፤ ለመታዘብ መከልከል እንዲሁም ከድምፅ መስጫ ቁሳቁስ እጥረት ጋር የተያያዙት ክስተቶች ይገኙበታል። ይህ ሪፖርት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እንዲሁም የምርጫ ጣቢያዎች ቅድመ ዝግጅትን ብቻ የተመለከተ ሲሆን፤ የድምፅ አሰጣጥ እና የቆጠራ ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ያሉትን ሁኔታዎች መታዘቡን ይቀጥላል። በተጨማሪም አፋጣኝ መፍትሄ የሚያሻቸውና ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ አሳሳቢ ኹነቶች በሚከሰቱበት ወቅት ህብረቱ ለምርጫ ቦርድ በማሳወቅ መፍትሄ እንዲያገኙ እየጣረ ይገኛል።

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች የምርጫ ጣቢያዎችን አከፋፈት እና አወቃቀር በተመለከተ ከታዛቢዎች እስከአሁን ድረስ በተሰበሰበ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ህብረቱ ተገቢውን መረጃ ካሰባሰበና እና ካጣራ በኋላ በዚህ መግለጫ ላይ የተካተተውን መረጃ ጨምሮ በድምፅ አሰጣጥና በቆጠራው ሂደት ላይ አጠቃላይ መግለጫ ነገ መስከረም 21፣ 2014 ዓ.ም እንደሚሰጥ ለመግለፅ ይወዳል።

በመጨረሻም፤ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ህብረት ለምርጫ፣ ዜጎች የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱን እና የቆጠራ ውጤት በትዕግስት እንዲጠባበቁ ጥሪውን ያቀርባል።

*የምርጫውንም ሂደት ሆነ ህብረቱን የሚመለከቱ ተከታታይ መረጃዎችን ለማግኘት የህብረቱን ድረገጽ፣ የፌስቡክ እና የትዊተር ገፆች ይጎብኙ*

*ለተጨማሪ መረጃ የህብረቱ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ዬሴፍ መኮንንን* ***0913923542*** *ያግኙ የኢሜይል አድራሻ* ***info@cecoe.oeg***